# ፋይዳ ቢስ ተቃዋሚ

በተጋድሎ ሐርነት ህዝብ ትግራይ ህገመንግስት መሰረት ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት የወያኔን ስልጣን እስከ አልተቀናቀነና ይህን ጠባብ የአንድ ጎጥ ጉጅሌ አክብሮና ያለውን ስርአት አወድሶ እስከ ሰራ ድረስ ጤነኛ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ድርጅት ተብሎ ዳረጎቱን እየተቀበለ ከወያኔ ጋር ሰምና ወርቅ ሆኖ ለመሄድ ምንም ችግር እንደ ማይገጥመው የታወቀ ነው። እነማን ተቸገሩና ፣ እነማንስ ተሰቃዩና ፤ እኛስ በዚህ ውስጥ ገብተን ወያኔን ለማማት የምንሞክረው ። ዴሞክራሲ ዓለም አቀፋዊ መሆኑ ቀርቶ በወያኔ አምሳል ሲቀረፅና ሲተነተን ፣ የኢትዮጵያ አድርባይ ፖለቲከኞች ፤ ይህ አይነቱን ዴሞክራሲ ይሁንብን አሜን ብለው ሲቀበሉት እንዲያ ነው ትግል እንዲያ ነው ህዝባዊ ዴሞክራሲ ብለን ልናልፈው አንችልም ። በህዝብ ስም እነታገላለን ብለው ተነስተው የህዝቡን ትግል ሲያሽመደምዱት በይሉንታና ድርጅታዊ ሰላምን (organizational peace) ለመፍጠርና አለታዊ የድርጅት ጥቅም ለማግኘት ሲባል የተመጻዳቂነት ፖለቲካን ዝም ብለን ብናልፈው በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ደባ ከመስራት ያለፈ ነውና ለነዚሁ ድርጅቶች ጥፋት ፤ አባሪና ተባባሪ ልንሆን አይገባም ።

እነዚህ ድርጅቶች ከጠላት ጋር የያዙት የትብብር ጉዞ አደገኛነቱ ድርብ ድርብርብ ስለሆነ፣ የሚያመጣው ጉዳት በራሳቸውና በአባሎቻቸው ብሎም በደጋፊዎቻቸው ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም ፡፡ አንድ ድርጅት እንቅስቃሴውን በሚመለከት አንድ ውሳኔ ወስኖ ተግባራዊ ሲያደርግና ፣ ይህም ውሳኔ ህዝባችንን በቀጥታ የሚመለከት በሚሆንበት ወቅት ፣ ወደድንም ጠላንም ሁላችንም የችግሩ ተካፋዮች ነንና ይመለከተናል ። እንደዚህ የመሰሉ የፖለቲካ ውሳኔዎች የምንታገለውን ጠባብ ብሄርተኛና ጎጠኛ አገዛዝ ስርአት ህዝባችንን ለመደብደብና ለማጎሳቀል የበለጠ የፖለቲካና የሞራል ድጋፍ ከመስጠቱም በላይ ለሚፈልገው ዓለማቀፋዊ ድጋፍ በቀጠታ አስተዋፅዖ አለው፡፡ እኛም "የፋለትትን ማድርግ መብታቸው ነው" በሚባለው ያለቦታው በተደነቀረና እንደፈለጉ በሚንሸራተቱበት የተልባ መብት ሙግታቸው ልንሞግት ቀርቶ ለማዳምጥም ጊዜ ማባከን አይኖርብንም ። ስለ ዴሞክራሲና ድርጅታዊ መብት ከመወራቱ በፊት ስለ አንድ ሀገር ሉዐላዊነትና ዴሞክራሲ ፤ ድርጅታዊ ግዴታና ህዝባዊ ሀላፊነትን ጠንቅቆ ማወቅን ይጠይቃል። ይህን ሳያሰምሩ በህዝብ ጀርባ ተንጠልጥለው ስለ መብታቸው የሚያደርጉት ክርክርና ጫና በላያችው ላይ የጥፋት ዘመቻን እየጋበዙ እንደሆነ ረስተው እንደ ሎጥ ምሽት ቁመው ይቀራሉ ።

የተጋድሎ ሀርነት ህዝብ ትግራይ ፣ ወያኔም በመጭው ምርጫ ሊያስመዘግብ የሚፈልገው ይህንኑ ስለሆነ ፣ እነዚህ ኢትዮጵያዊ ነን እያሉ የህዝቡን ትግል በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ትግሉን ወደ እማይሆን አቅጣጫ ሲወስዱት ፤ በህዝባችን ላይ ምን ዓይነት ደባ እየተሰራበት መሆኑን ማብራራትና ማስረዳት ከማንኛውም ለህዝብ ቆሜአለሁ ከሚል ኢትዮጵያዊ ታጋይ ሁሉ ይጠበቃል ። ይህ ደግሞ በድርጅቶች ውስጥ ለታቀፉና ለደጋፊዎቻቸው ጭምር አመራሮቻቸው የወሰዱትን እርምጃና እንቅስቃሴ ምን ያህል ጎጅ እንደሆነ ከአሁኑ አበክረው እንዲያዩት ፤ እንዲወያዩበት ይረዳል። ሁኔታዎች ካለፉና ነገር ካለቀ ከደቀቀ በኋላ ብናወራው ለተናጋሪውም ሆነ ለሰሚው ጠቀሜታ አይኖረውም ።

ይሁንና ተቃዋሚዎች በአሁን ሰአት ወደ ወያኔ ምርጫ ለመግባት የሚያቀርቡልንን መከራከሪያ ነጥቦች እንመልከታቸው ።

<u>በምርጫ መሳተፍና ወያኔን ለማጋለጥ አስፈላጊነቱን ያነሳሉ ፣</u> ይህ የማጋለጥ መፈክር የታክቲክ መፈክር ነው።

በምርጫው መሳተፍ ወያኔን ለማጋለጥ ይረዳል የሚል ያረጀና አምስት አመት ያለፈው ክርክር በተደጋጋሚ እነዚሁ ድርጅቶች እንደ መከራከሪያ ነጥብ ሲያነሱ ይሰማሉ ። ለዚህ የሚኖረን መልስ አጭርና የማያዳግም ይሆናል ። መፈክሮች ሲነሱ ያለውን ተጨባጭ እና ሊሆን ከሚችል ሁኔታ ቢያንስ ጊዜአዊ የፖለቲካ ጥቅም ሊያመጣና መሰረታዊ የትግሉን አላማ ሊያራምድ ይችላል ከሚል ግንዛቤ በመነሳት ይሆናል ። ይህ ሁኔታ ሲያልፍና ጠላትም ከዚያ ጊዜያዊ ሁኔታ ሲያመልጥ በጊዜው የተነሳው መፈክር የረጅሙን ጊዜ ትግል የሚደግፍ የታክቲክ መፈክር ነውና ከተለዋጩ ሁኔታ ጋር አብሮ ተለውጦ ጊዜውን የሚያንፀባርቅ አዲስ መፈክር ይወጣል ።

ይህን ለማየት አለመቻል በድርጅት ደረጃ አለመብሰልን ፣ የጠላትን ሁኔታ አለመረዳትን ያመለክታል ። ይህ ደግሞ ጠላትን ከመናቅ ፣ አለዚያም አጥብቆ የጠላትን ኃይል ከማጋነን የተነሳ ይሆንና ለትዕቢት ወይም ለፍርሃት ምንጭ በመሆን ታክቲኩ ስተራቴጅውን የመዋጥ አደጋ ብሎም የአስተሳሰብ ቀውስ ይፈጥራል ። በዚህም ምክንያት መላው ድርጅቱ ለከፍተኛ አደጋ ፣ ለጠላት ዱላ ፣ የተጋለጠ ይሆናል ። ጠላትን መናቅም ሆነ መፍራት አደጋው ተመጣጣኝ ነው ። እነዚህ ድርጅቶች ጠቅላላ አቀጣጫቸውን ስተው ሁሉም ነገር ስትራቴጂ ሁሉም ነገር ታክቲክ ሆኖ ሲመሳቀል በመሰረቱ ሰትራቴጂ የሚባል የለም ማለት ነው ። ሁሉም ነገር ታክቲክ ሆኗል ። የቻይናው የጦር ሊቅ ሰን ጹ (SUN TSU) ከክርስቶስ ልደት በፊት በ500 ኛው ክፍለ ዘመን ገደማ THE ART OF WAR በተባለው መፅሐፉ እንዲህ ይላል "Strategy without tactics is the slowest route to victory. Tactics without strategy is the noise before defeat."

በ97ቱ (2005) በተደርገው ምርጫ ፡ የተጋድሎ ሀርነት ህዝብ ትግራይን መንግስት በሁሉም አቅጣጫ እርቃነ ስጋውን መጋለጡ ብቻ ሳይሆን በወያኔ መንግሰት ላይ ብዥታ ፡ በኢትዮጵያ ህዝብ የፖለቲካ ብስለት ላይ ጥርጣሬ ለነበራቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች የማያዳግም ትምህርት አስተምሮ ፤ በወያኔ ጠባብ ጉጠኛ ስርአት ስር የምርጫ ፖለቲካ የሚባል ፈሊጥ ትግሉን የሚያዘናጋ ፤ አሳሳችና አደገኛ መሆኑን በማያዳግም መልኩ አስተምሮናል ። በጊዜው ተይዞ የነበረው ታክቲክ "ወያኔን ለማጋለጥ ምርጫ መሳተፍ" የሚለው መፈክር ግንቦት 7 የምርጫው ሰዓት አልቆ ጣቢያወቹ ሲዘጉ መፈክሩም እዚያው ላይ ታሪካዊ ሚናውን ጨርሶ አክትሟል ። ይህን ያለፈበት መፈክር አንግቦ አሁንም "ወያኔን ለማጋለጥ ምርጫ ውስጥ መሳተፍ" አለብን የሚል ክርክር እንደ ተጀመረው ከቀጠለ እንዳልነው እርቃነ ስጋውን የቀረውን ወያኔን ለማጋለጥ ሳይሆን እራስ -ሲመለጥ አይታወቅ- እንደሚሉት እራስን በሁሉም አቅጣጫ ለማጋለጥ የሚደረግ ጥረት ይሆናል ። ካለፉት የፖለቲካ ታሪካችን ግንዛቤ አለመውሰድ በፖለቲካው ረገድ ከዚያ ግድያና እስራት ፡ ግርፋት በኋላ አለመማርና አሁንም ወያኔን በመናቅ እንበለው በመፍራት እያንዣበበ ያለውን አደጋ ለማየት ካለመቻላቸው አልፎ ፤ ተነሳን የሚሉበትን የትግል መስመር እንኳን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማስረዳት ተስኗቸዋል ። የታክቲክ መፈክር እድሜ ምን ጊዜም ከመስከረም አደይ አበባ ወይም ከዝንብ እድሜ ያለፈ አይደለም ። ወያኔ ከመጋለጥ አልፎ አፅሙ ብቻ የቀረ ስለሆነ ማጋለጥ የሚለው ቋንቋ እራስን ማታለል ይሆናል።

በአለፉት 18 አመታት በሀገራችን ውስጥ በደረሰው የፖለቲካ የኤኮኖሚ የማህበራዊና ባህላዊ ቀውስ የፈጠረውን ውዥንብርና አደጋ ዞር ብለን ለማየት ባለመቻላችንና በተደራጀ መልክ ለማጥቃት ቀርቶ ለመከላከል እንኳ አልፎ አልፎ ከሚሰነዘሩ ግብታዊ አስተያየቶች በስተቀር የተቀናጀና መሰረትን ለማስያዝ የተደረገ ጥረት የለም ። ይህም በመሆኑ ቢያንስ በትግል ላይ ሆነን ኢኮኖሚውን መለወጥ ባንችልም ፡ በስነ ልቦና ዝግጁነትና በፖለቲካ አስተሰባችን ላይ ጠላት ሊፈጥር የሚችለውን የአስተሳሰብ ተፅዕኖ ለመዋጋት መቻል ነበረበት ። የአንድን ህዝብ ስነ ልቦናና የፖለቲካ አስተያየትን ለመለወጥ ጠላት በተለያየ መንገድ ከህዝቡ ድጋፍ ለማግኘት የተለያዩ ጥረቶችን ያደርጋል።

በዚህም የጥረቱ ዘመቻ በድርጎና በመቅኑን የአኮኖሚ ድጎማ በማድረግ ህዝቡን ወደ እሱ ለማቅረብ ሲያቅተው ወደ ወታደራዊና ፖለቲካዊ የማጥቃት ፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ይገባል ። መንግስታት ባገር ውስጥ

ውጥረት ሲበዛባቸው የሌለ የውጭ ወራሪ ጠላት ፈጥረው በህዝብ ላይ የሽበር ዘመቻ ፤ በተቃዎሚዎች ላይ የጠላት ተባባሪ ናቸው በማለት ያስራሉ ፤ ያፍናሉ እንቅስቃሴያቸውንም ይገታሉ ፤ አልፈው ተርፈውም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃሉ ። የህዝቡን ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ ፤ የመናገር ፤ የመጠየቅ ፤ የመቃወም ብሎም መሰረታዊ ሰብአዊ መብቱን ይገፋሉ ይረግጣሉ ። ለፀጥታ ለስለላ ለወታደራዊ እርምጃ ገንዘብ ማግኝያ ዘዴ ሲባል ያለአግባብ የገበያ ዋጋ እንዲንር ይደረጋል ። እነዚህን የመሰሉ ከስተቶች በመላው አለም መንግስታት የሚጠቀሙባቸው ፀያፍ የአስተዳደርና የአገዛዝ ባሕሪያት ናቸው ።

ሆነና በትግሉ ተዋንያን በኩል ሊደረጉ የሚችሉና የትግሉም አንድ ምዕራፍ ሆኖ መታየት የነበረበትን የባህል ዝቅጠቱንና ጠላት በኛ ላይ ሊያሳድር የሚችለውን የፖለቲካና ያስተሳሰብ ተፅዕኖ የመዋጋቱን ተግባር ችላ ተብሏል ። ወይም መረዳት ተስኗቸዋል ። በመሆኑም በስነ ልቦና በዝግጅትና በፖለቲካ አሰተሳሰባችን ላይ ይህ ነው የማይባል አደጋ ላይ እየደረሰ ነው ። ይህ ደግሞ በትግሉ ላይ ተፅእኖ እንዳለው እያየነው ነው ። የተነሱትን ችግሮች ብስል ተቀሊሉን አበጥሮ ለማየት ድርጅቶች እራሳቸው የነቃና የበሰለ የፖለቲካ አመራር እጦት የዚህ የጠላት ፕሮፓጋንዳ ሰለባ ሆነው ጠላት የሚያናፍሰውን ማስፈራሪያ እንደ እውነታ ተቀብለውና አምነው የድርጅት እንቅስቃሴአቸው ሙሉ በሙሉ ግራ ተጋብቶ እናየዋለን ። አንደኛውን እናንሳና እንየው ፣

ይህ የተጋድሎ ሐርነት ሕዝብ ትግራይ ኅጠኛ ጉጅሌ በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ሲያጣና የመውደቂያ ጊዜው ደርሶ በተንገዳገደ ቁጥር እኔ ከስልጣን ከተወገድኩ በአገሪቱ ውስጥ የእርስ በርስ እልቂት(ኢንተርሃሞዌይ) ይነሳል ፤ ስለሆነም አትንኩኝ በሚል ሁልጊዜ ሲያስፈራራ ይታያል ። ድርጅቶችም ይህን እንደ ሀቅ ተቀብለውና አምነው ሲያስተጋቡት ይገኛሉ ። ያለኔ ኢትዮጵያ ትጠፋለች ፣ የእኔ መኖር የኢትዮጵያን መኖር ያበስራል ፣ የኔ አለመኖር ግን የአንድነቷን ሁኔታን አጠያያቂ ያረግዋል ፣ የሚለው የስልጣን ጥመኞች አባባል በሀገራችን ውስጥ ሲነሳ ዛሬ የመጀመሪያው ጊዜ አይደለም ።

<u>የጎሳ እርስ ባርስ ብጥብጥ (ኢንተርሃምዌይ )</u>

ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም ፤ ነብሳቸውን ይማርና ፤ አፄ ኃይለ ሥላሴ ከመንገሳቸው በፊት ጀምረው በቅርብ ያውቋቸው ስለነበረ ለመንገሳቸውም ትልቅ አስተዋፅዖ እንዳደረጉ በህይወት ታሪካቸው በፃፉት መፅሐፍ ውስጥ ያነሳሉ ። ፊታውራሪ ከንጉሡ ጋር ባደረጉት ጭውውት ያዘኑበትንና በንጉሡ ላይም ከፍተኛ ጥላቻ ካሳደረባቸው አንዱን የሀገር ጉዳይ እንዲህ ሲሉ ያነሱታል ፤

አንድ ቀን ስንነጋገር እንደዚህ አሉኝ <u>"አንተ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ የምትለው ፤ ኢትዮጵያ ያለ እኔ ምንም አይደለችም ፤ ዕድልዋ ከኔ ጋር የተሳሰረ ነው ። እኔ ነኝ የማደርሳት ። ካለኔ ትኖራለች ብለህ አታስብ ።"</u> አሉኝ ።'

"እንደዚህ በድፍረት ሲናገሩ በጣም ተገረምኩና ተበሳጨሁ ። እንዴት እንደዚህ ያስባሉ? ኢትዮጵያኮ ሕያው ነች! እኛ ሁላችንም ዐላፊዎች ነን ። ኢትዮጵያ ግን አታልፍም ። እስቲ ይመልከቱ! ዐፄ ምኒልክ ዛሬ የት ናቸው? አባትዎ ራስ መኮንን የት አሉ? ሌሎቹስ ታላላቆችና ገናናዎች የነበሩት ሁሉ የት ናቸው? ኢትዮጵያ ግን አለች ። ወደፊትም ትኖራለች አልኳቸው ። ነገሬን ሊቀበሉ አልፈቀዱም ። <u>"ኢትዮጵያ ያለኔ ትኖራለች ብለህ አታሰብ</u> አሉኝ ፡፡ ከዚያ ወዲህ በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ላይ የነበረኝ አስተያየትና ስሜት ሁሉ ተለወጠ ።" አቶ ባዮግራፊ (የህይወት ታሪኬ) ፊታውራሪ ተክለ ሃዋሪያት ተክለ ማርያም መግቢያ ገፅ xviii ላይ ።

እዚህ ላይ የተክለ ሀዋርያን ማንነት ለማንሳት ሳይሆን ንጉሡም በጊዜአቸው ህዝቡ ተገዥ እንዲሆን የንጉሠ ነገሥቱን አገዛዝ መቀበል አለመቀበል ከኢትዮጵያ ጋር እያይዘው ሲያስፈራሩበት እንደኖሩና እኛም ከልጅነት እስከ እውቀት አምነንበት እንደኖርን ትዝታችን ነው ። ገዥዎች የኢትዮጵያን አንድነት ህዝብን ለመግዛት የማስፈራሪያ መሳሪያ አድርገው መጠቀም የነበረና ያለ ዘዴ ነው።

ወያኔ ከስልጣን ቢወገድ ኢንተርሀምዊይ (የህዝብ መተላልቅ) ይኖራል ቢለንና እርሱንም ተከትለው በፍርሀት ፤ መቀመጫቸው ቄጠማ የሚቆርጠው ስለ ኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ የማያውቁት ቢኖር በጣም ትንሽ ወይም ምንም ነገር አለማወቃቸውን ነው ። የኃይለ ሥላሴ መንግስት ከስልጣን ሲወገድ ህዝቡ እርስ በርስ ሲተላልቅ አላየንም ። እንዲዚያውም ሁሉ ከደርግ በኋላም የወያኔ ጦር ሰተት ብሎ አዲስ አበባ ሲገባ ያለምንም መሪና ቀስቃሽ ሳይኖረው ከተማው ስርአት እንዳያጣ ሲል ሕዝቡ ግጭት አላነሳም ። ሌላው ቀርቶ ሌባውና ወሮባለው ፤ ማጅራት መቺው እንኳን ለዘረፋ አልተነሳም ።

ከ18 አመት በፊት ህዝባችን ያስመዘገበውን አንድነትና ሰላም አንዱ ለሁሉም ሁሉም ለአንዱ በመተሳሰብ የከተማውንና የአገሪቱ ፀጥታ በማስከበር አንድነቷን አስጠብቋል ። የተቀዋሚ ድርጅት ነን የሚሉት የትላንትናውን ታሪክ ማገናዘብ ተስኗቸው ፤ ለህዝቡ ባዕድ በመሆን የተጋድሎ ሐርነት ሕዝብ ትግራይን የመጨረሻ ማስፈራሪያ ፕሮፓጋንዳ ተደጋግሞ ሲነገራችውና በውጭ መንግስታትም እንደማስጠንቀቂያ ሆኖ በየጊዜው በየኤምባሲው በሚደረገው ስብሰባ ለሚቀርቡት አጀንዳዎች የማስፈራሪያና ማሳመኛ ምክንያት እየሆነ ስለሚነገራቸው በሚያሳዝን ሁኔታ አምነው ተቀብለውት ወያኔ ይህን እንዳይፈፅም ተንበርክከው ሲማፀኑት ይታያሉ ። እናት ልጇን ስታፅናና "ፈሪ ለናቱ" አለች እንጂ ፣ አርበኞች አባቶቻችን አገራችንን ለማስከበር ሲዋደቁ ስለ ፈሪ እንዲህ ነበር ያሉት ፡-

ደፋር ይሙት ፡ ፈሪ ይኑር ቢሻው ፤<br>አተላ መሸከም ፡ ይችላል ትክሸው ።

ስለሆነም በወያኔ ፕሮፓጋንዳ ያን ያህል ስለአመኑና ስለፈሩ ፤ የወያኔ መገርሰስ ምፅአት ፤ የዓለም ወይም የኢትዮጵያን አርማጌዶን <u>AN ETHIOPIAN ARMAGEDDON</u> እንደሚመጣ አርገው አምነዋል ። የኢትዮጵያ አርማጌዶን የሚመጣው በወያኔ አገዛዝ ስርአት መቀጠል እንጅ ፤ በተጋድሎ ሐርነት ህዝብ ትግራይ ህገመንግሥት መፋቅና በህዝባዊ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ አንድነት ላይ የተዋቀረ ህገመንግሥት ህዝቡ መክሮበት ዘክሮበት በሚታወጅ ፤ ህዝቡም በህገመንግሥቱ መሰረት በድምፁ ሊያወርደው ፤ ሊያወጣው ፤ ሊሽረውና ሊቆጣጠረው የሚችል መንግስት መርጦ ሲያስቀምጥ አይደለም ። ያ ቀን ሲመጣ ወያኔ ሲነኮታኮት የኢትዮጵያ ህዝብ የበለጠ ይተባበራል ። እጅ ለእጅ ተያይዞ ወንድማማችነቱን እንደ ገና ያበስራል እንጂ ወያኔ በመሄዱ የኢትዮጵያ አርማጌደን ይመጣል ብሎ አይፈራም ። ለህዝብ ቆመናል የሚሉን ይህ አይነት አስተሳሰብ በህዝብ ዘንድ በትንሹ ቢኖርም እንኳ ( even if there exists such a belief ) ተቀባይነት እነዳይኖረው ፀረ ወያኔ ፕሮፓጋንዳና ትምህርት ከማስተማር ይልቅ ይባስ ብለው "አልቅሳ ታስለቅሰኛለች" እንዳለው ፈሪ አያ ባል ኩራቴ ፤ እራሳቸው ፈርተው ህዝባችን የፍርሃታቸው ተካፋይ እንዲሆን ይጋብዛሉ ። ወያኔም የሚፈልገው ይህ ጥረት የተሳካ እንዲሆንና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነትን እነዲያገኝ ማድረግ ሲሆን ፤ይህ ጥረቱ እንዳይሳካ መኢአድ ዘው ብሎ መለጠፉን ህዝብ ማወቅ አለበት ። ሀላፊነትን መዘንጋት አንድ ነገር ነው ፣ የጠላት መሳሪያ መሆን ግን በደንብ ያጋጨናል ። ይህ ጉዳይ በህዝብ አዕምሮና አስተሳሰብ ውስጥ እንዳይሰርፅ ማስተማርና የጠላትን የዉሸት ቅኝት ማጋለጥ ፤ ራስን ከዚህ ሙልጭልጭ ፖለቲካ ነፃ ማድረግ አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት ወገባቸውን እየስበቁ ትክክል ነን ብለው መኢአድንም ሆነ ሌሎችን ኮልኮሌአሞች ያለምንም ምህረት እናጋልጣለን ። ለዚህም ነው "እኛም አውቀናል ጉድጓድ ምሰናል" ኢትዮጵያ በልጆቿ ትታነፃለች የምንለው ።

አሁንም ወያኔ ተጠራርጎ ገደል ቢገባ የኢትዮጵያ ህዝብ እልልታውን ያቀልጠዋል እንጂ ጦር ተማዞ እርስ በርሱ ይተላለቃል ለማለት የሚያስደፍር ምንም አይነት ፍንጭ አናይምም ፣ አይኖርምም ። የኢትዮጵያን ህዝብ አስተዋይነትና ጥበብ ፣ በተለይም በአሁኑ ሰዓት ያለውን የፖለቲካ ብስለት ፤ ለሀገር አንድነትም ያለውን ፍቅር ዝቅ አርጎ ማየት በድርጅቶችና በኢትዮጵያ አስመሳይ ፖለቲከኞች ሊፈፀም የማይገባው ታሪካዊ ስህተት እየተሰራ ነው ። ለምን ቢባል ህዝቡ ከኛ የላቀና የረቀቀ የነቃ መሆኑን መቀበል ስለ አቃተን ነው ። ቀጣፊ ነጋዴ በሚሸጠው የእቃ ጥራት ሳይሆን በምላሱ ብቻ ስለሚተማመን ሁል ጊዜ ገበያተኛውን እንደሞኝ ስለሚቆጥር የራሱን ባዶነት የሚረዳው ገበያው ሲበተን የሚገዛው አጥቶ ኮሾ እቃውን ጠቅልሎ ኪሳራ በኪሳራ ሆኖ በእዳ ሲያዝ ነው ። የኛም ዋጋ ቢስ ተቃዋሚዎች ለኢትዮጵያ ህዝብ ሊሸጡ ያቀረቡት ፖለቲካ አያ ድቡልቡሌ ሆኖ ፡ ከስሮ ፤ በዕዳ ከተያዘ ወራት እያለፉት ነው ። ጠላትን

**መታገል ማለት ኳስ ሜዳ የሚደረግ ግጥሚያ አይደለም ። ወያኔ ተሸንፎ እስከ ሚወድቅ ድረስ ድርጅቶችን ለማጥቃት ህዝቡን ለማስፈራራት የማይጠቀምበት መላ የለም ። እየተከታተሉ ማክሸፍ ህዝቡን ማስተማርና ማጠናከር የድርጅቶች ተግባር ይሆናል ።**

**ኢትዮጵያ ውስጥ መበጣበጥ ከተነሳ በራሱ በወያኔ ውስጥ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው ። በመግደል የተመሰረተ ቡድን የሚያከትመው እርስ በርሱ በመገዳደል ነውና ። ጅቦች የሚበሉት ሲያጡ እርስ በርሳቸው ይበላላሉ ።**

**ድርጅቶች አሁን እየተሸመደመዱ ባሉበት ሰአት የተጋድሎ ሐርነት ህዝብ ትግራይን የግብረገብነት ሰነድ ተቀብለው እነደ አሰርቱ ቃላተ ወንጌል ፅላተ ሙሴ አሰርተው በሚሰግዱበት ወቅት የነሱ ሐዋርያት አስመሳይ ምሁሮች** (Pseudo Intellectuals) **የመከራከሪያ መሳሪያ አርገው ፣ ማር እሰጥ አገባ ሲሉ እየሰማናቸው ዞር ብለው ከናንተ ጋር ልዩነት የለንም ፤ ነገር ግን ይሉናል ፤ “በሀገሪቱ ላይ አንዣቦ ያለው አደጋ አገሪቱ እንዳልነበርች የምትሆንበት ፤ ሁላችንም አገር የምናጣበት ጊዜ ነው” ይኸ መናጢ ወያኔ... ይሉና የአዞ እንባቸውን እንድንጠርግላቸው ከንፋራቸውን ይመጡልናል ። በዚህ የሚሉትን ብጥብጥ እንየው ። በብጥብጡ ዋና ተካፋይ አርገዉ የሚያዩት የትግራይን ህዝብ ነው ፡፡ የትግራይ ህዝብ የሚለው አባባል አለ “ዝበረቐ ፀሀይ ይሙቐና ዝነገሰ ንጉሥ ይግዝአና” ይላል ። የወጣ ፀሃይ ይሙቀን ፤ የነገሠ ንጉሥ ይግዛን ማለት ነው ። ወያኔ ሲንኮታኮትና ሲወድቅ ወያኔዎችን አምኖ እንደተጠሉና እንደማይፈለጉ እያየ ብቻዉን ጦር ይዞ ከቀረው የኢትዮጵያ ህዝበ ጋር የሚዋጋበት ምንም የክርክረ ተዋረድ ሊኖሩ አይችልም ። ባለፈው ምርጫ ወቅት አንድ የትግራይ ሰው እራሳቸው ለጢብ መቆሰቆሻ ለሚሉት የኢንተርሀምዌያቸው ታከቲክ እውነተኛ ነው ለማለት እራሳቸው ገድለው ፤ ትግሬ በመሆኑ ህዝብ ገደለው ብለው ሲለፍፉ ያለምንም ጥርጥር አዎ ብለው የተቀበሉት ተቃዋሚ ነን ባዮች ነበሩ ። እነ አረጋዊ በርሄና ሌሎችም ። ለማጣራት የወሰዱት ጥረት አንድም አልነበርም ። ምክንያቱም በሽታቸው በእለት ተእለት በወያኔ የእድሜ መግዣ ታከቲክ የተጠመደ ነውና ። ይህ ስነ ሀሳብ ከማጠቃለላችን በፊት በአጭር ጊዜ የጠላት አሉባልታ ተፈተን ያን አሉባልታ ከማስፋፋት ይልቅ ፣ ለረጅሙ ትግል መዘጋጀት ይኖብናል ፣ በታሪክ አተላዎች እንቶ ፈንቶ ተውጠን ጊዜያችንን እናባክንም ። ለህዝባች ግን እውነታውን ከመናገርና ከማስረዳት መጋለጥ ያለባቸውንም ከጥላቻ በነፃ እናጋልጣል ። በህዝባዊ ስራቸው ከፍ ማድረግ ያለብንን ከፍ ከፍ እናረጋቸዋለን ። ከህዝብ ሥራ ሲርቁና ከጠላት ጋር ሲሞዳሞዱ ደግሞ ተገቢውን ዝቅተኛ የአተላ ቦታ ያገኛሉ ። ታማኝነታችን አሁንም ለኢትዮጵያ ህዝብ ነው ። አሁንም ሆነ ወደፊት በዚህ አንፃር ተስተካክሎ የማይሰለፍ የወያኔን የምርጫ ግብረገብ ሰነድ ከፈረሙትና ወደ ምርጫ ለመግባት እየፈለጉ ቁርጠት ይዞአቸው ለሚንከባለሉት ሁሉ ተግባራቸው በህዝብ ፊት የተጋለጠ ይሆናል ። ከህዝብ የተደበቀ ነገር የለንም ። የኢትዮጵያ ህዝብ ከሁላችንም ይህን ይጠብቃል ። በመደምደሚያችን ይህን ብለን እንዝጋው ፤**

If you know the enemy and know yourself, you need not fear the result of a hundred battles. If you know yourself but not the enemy, for every victory gained you will also suffer a defeat. If you know neither the enemy nor yourself, you will succumb in every battle. -

The good fighters of old first put themselves beyond the possibility of defeat, and then waited for an opportunity of defeating the enemy. To secure ourselves against defeat lies in our own hands, but the opportunity of defeating the enemy is provided by the enemy himself. Thus the good fighter is able to secure himself against defeat, but cannot make certain of defeating the enemy.

- Sun Tzu

**ኢትዮጵያ በልጆችዋ ትታነፃለች**
**ከእያዩ ቢወጣ**